የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር - ዴሞክራሲያዊ ምትሕብባር ትግራይ
TIGRIAN ALLIANCE FOR NATIONAL DEMOCRACY (TAND)
e-mail: ezanareg@hotmail.com

የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር የ"አልጀሪሱ ውል"ን ይቃወማል! ጥናታዊ -ምክክር እንዲደረግ ይጠይቃል!!

የኢትዮጵያና የኤርትራ ድንበርን አስመልክቶ ከ16 ዓመታት በፊት በአልጀሪስ የተፈጸመው ደባ በሁለት ዲክታተሮች መካከል የተደረሰ ስምምነት እንጂ ህዝቦቻችንን እንደማይወክል ከዚህ በፊት ደጋግመን ግልጽ አድርገናል። ይህ ህዝቦቻችንን የማይወክል የ"አልጀሪሱ ውል" እንዳለ አሁን በዶክ/ አብይ የሚመራው መንግስት ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩ ስንሰማ ከልብ አዝነናል። እንድንቃወምም ግድ ሆኖብናል።

ስልጣን የተረከበው አዲሱ የኦህዴድ ሓይል ህወሓት/ኢህአዴግ እስካሁን ድረስ የተጓዘበትን ጸረ-ሃገርና ጸረ-ህዝብ መንገድ ቀልብሶ፣ ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማሸጋገር የጀመረውን ፈታኝ ትግል በጥሞና መከታተል ብቻ ሳይሆን ይበል – ግፉበትም በማለት ስናወድስ ሰንብተናል። በቅርቡ የመለስ ዜናዊ ሁለቱ ብትሮች "በክብር" ሰባብረው ማስወገዳቸውን ስናይም ዴሞክራሲያዊ ሂደቱ ያለአደናቃፊ ይበልጥ ይፋጠናል የሚል ተስፋ ማሳደራችን እውነት ነው። ሆኖም አሁን የ"አልጀሪሱ ውል" አስመልክቶ የደረሱበትን ውሳኔ ስንመለከት ግን የቆየውን ስሕተት እንደማረም ፈንታ ያንኑ ስሕተት ደግሞ መቀስቀሱ ለምን አስፈለገ የሚል ጥያቄ እንድናነሳ አድርጎናል።

ከመጀመርያው የ"አልጀሪሱ ውል" ሲጸነስ ከህዝብ በስተጀርባ በድብቅ የተወጠነ ነበር። የኢትዮጵያ ህዝብ አያውቀውም፣ እውቅናም ነፍጎታል። የሃገር ድንበርን ያህል የሉዓላዊነት መግለጫ ወሰን፣ በዛው ላይ አያሌ ዜጎች መስዋእት የሆኑበት የማንነት ሰንደቅ፤ እንደተራ የፖሊሲ ውሳኔ ታይቶ በአንድ ፓርቲ ወይም መንግስታዊ አካል የሚወሰንና የሚከናወን ጉዳይ አይደለም። ትውልድ ደም የከፈለበትና ወደፊትም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እንደገና ህዝቡ ደሙን የሚከፍልበት ቅርስ ስለሆነ ያለ ህዝቡ ተሳትፎ ውሳኔ ላይ መድረስ የቸግሩን ክብደት በውል አለማጤን ያመለክታል። በተጨማሪ በዚህ አሳሳቢ ጉዳይ ላይ ሰፊ ጥናት ያካሄዱና ጥልቅ እውቀት ያካበቱ ሃገር ያፈራቻቸው የታሪክ፣ የሕግ፣ የመልከአ-ምድር፣ ወዘተ ባለሙያዎች መጠቀምም የግድ አስፈላጊ ሆኖ እያለ ከዚህ አሰራር መራቁ ሌላው ትልቁ ስሕተት ነው። ያለ እነዚህ ዓይነቶቹ ሃገራዊ ባለሙያዎች ተሳትፎ የተካሄደና ወደፊትም የሚካሄድ ድርድር ካለ ለሃገራዊ ክስረት መዳረግ መሆኑ መገንዘብ አስፈላጊ ነው እንላለን።

የ"አልጀሪሱ ውል" አሁን ከባድመ ጀምሮ እስከ ዓዲ-ኢሮብ፣ ከዛም አልፎ በባዳና በጸሮና አካባቢዎች ያለው የድንበር ጉዳይና የህዝቦቹ መብት ጥያቄ ለአንባገነኖቹ የፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ተድበስብሶ እንዲያልፍ በማቀዱ ያኔ ከባድ ተቃውሞ እንደቀሰቀሰ ሁሉ አሁንም ከድሮው በባሰ መልኩ ተቃውሞ ቀስቅሰዋል። ይህ ከባድ ህዝባዊ ተቃውሞ ጊዜ ሲረዝም ወደ ከፋ ትረምስ ሊያመራ ይችላል። ይህ አደገኛ ሁኔታ እንዳይከሰትና ሰላም እንዲሰፍን ከተፈለገ ከላይ የተጠቀሰው ግለጽና ሙያዊ የቸግሩን አፈታት መንገድ መከተል ፍጹም አስፈላጊ ነው።

ይህን ወሳኝ አመለካከት መሰረት በማድረግ ስልጣን ላይ የሚገኘው የዶክ/ አብይ መንግስት የሃገር ሉዓላዊነትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የባለጉዳዩ ህዝብ ድምጽ ማዳመጥ ብቻ ሳይሆን በየረድፉ ማሳተፍም ግድ እንደሚል እያሳሰብን፣ የመጨረሻውም ውሳኔ በህዝብና በዲሞክራሲያዊ መንገድ በተመረጠ ፓርላማ መወሰን አለበት እንላለን። በተጨማሪ ይህ ሃገራዊ ችግር ለዘለቄታው እልባት ያገኝ ዘንድ አንድ በቅድሚያ መደረግ ያለበት ነገር አለ እንላለን። ይኸውም ባለስልጣኑ መንግስት ከላይ የጠቀስናቸውና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ባለሙያዎች ያካተተ **ጥናታዊ -ምክክር** (ሂሪንግ / Hearing) ሁኔታው ሳይከፋ በተሎ እንዲካሄድ ነው።

ት.ዴ.ት. / TAND

10.06.2018